በፌዴራል ጤና ሚኒስቴር
የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
ዜና ኢሕጤኢ

ነሐሴ 2013 ቅጽ 5 ቁጥር 4

በኢሕጤኢ የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ቢሮ በየወሩ የሚዘጋጅ

# የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከኦሀዮ ዩኒቨርስቲ እርዳታ አገኘ



የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የሀገራችንን የበሽታ ቅኝት ስርዓት ለማጠናከርና ለማገዝ የሚረዱ ልዩ ልዩ ዴስክቶፕ ኮምፒተሮችን ከኦሀዮ ስቴት ዩኒቨርስቲ በእርዳታ አገኘ።

አቶ አስቻለው አባይነህ የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ም/ዋና ዳይሬክተር በንብረቶቹ ርክክብ ወቅት ባደረጉት ንግግር በሀገራችንም ሆነ በዓለማችን የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ከፍተኛ የሆነ የሰብአዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማድረሱን አውስተው ወረርሽኙ ከተከሰበተ ጊዜ ጀምሮ በሀገር ደረጃ ሁሉን አቀፍ የተቀናጀና ጠንካራ የመከላከል፣ የቁጥጥር እና ምላሽ ስራዎች በትኩረት ተግባራዊ በመደረጋቸው የሠው ሞት ቁጥር እና አገራዊ ቀውስ ከነበሩ ትንበያዎች አንጻር በእጅጉ ለመቀነስ ተችሏል ብለዋል። ለእነዚህ ውጤቶች መገኘትም መንግስት እና ሁሉም አጋር እና ባለድርሻ አካላት ለወረርሽኙ የሰጡት ትኩረትና የነበራቸው ቁርጠኝነት፣ ከፍተኛ ቅንጅት እና የህብረተሰቡ የነቃ ተሳትፎና ርብርብ ዋነኛ ምክንያቶች መሆናቸውን ም/ዋና ዳይሬክተሩ አስረድተዋል።

አቶ አስቻለው አያይዘውም በዛሬው እለት ከኦሀዮ ዩኒቨርስቲ በእርዳታ የተገኙት 75 ዴስክቶፕ ኮምፒተሮች የበሽታ ቅኝት ስርዓቱን ለማጠናከር እና የኮቪድ-19 ቅኝት ስራዎችን ከሌሎች የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ቅኝት ስራዎች ጋር በማቀናጀት ለመስራት እንደሚያግዝ ተናግረው በተለይም በጤና ተቋማት ያለውን የበሽታ የቅኝት ስራ ይበልጥ የሚያጠናክርና የመረጃ ፍሰቱን ለማሳለጥ እንደሚያግዝ አብራርተዋል።

ዶ/ር ደሳለኝ መንገሻ የኦሀዮ ስቴት ዩኒቨርስቲ ግሎባል ዋን ሄልዝ ኢንሼቲቭ የሪጅናል አድሚን ዳይሬክተር በበኩላቸው እርዳታው የሀገሪቱን የጤና የመረጃ ስርዓቱን ለማሻሻል እንዲሁም ኮቪድ-19 እና መሰል ወርረሽኞችን ለመከላከልና ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ያስችላል ብለዋል። ዳይሬክተሩ አያይዘውም ዩኒቨርስቲው ቀደም ሲልም በሁሉም ክልሎች ተመድበው የሚሰሩ 75 የጤና መረጃ ቅኝት ባለሙያዎችን ለኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በመቅጠር አጋርነቱን ማሳየቱን አውስተው በቀጣይም በአሁኑ ወቅት ዩኒቨርስቲው በልዩ ልዩ ዘርፎች እያከናወነ ያለውን አጋርነቱን አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

እነዚህ በዛሬው እለት ከኦሀዮ ስቴት ዩኒቨርስቲ በእርዳታ የተገኙት ዴስክቶፕ ኮምፒተሮች ለሁሉም ክልሎች እንደሚሰራጩ ለማወቅ ተችሏል።

# የጤና ስርዓቱን ለመደገፍ ሁሉን አቀፍ የተጠናከረ እቅድ መኖር ወሳኝ መሆኑ ተገለጠ

የጤና ስርዓቱን ወቅታዊና ታማኝ በሆነ ሳይንሳዊ ማስረጃዎች ለማገዝ እንዲቻልና ለችግሮች መፍትሔዎች ሰጭ ጥናቶችን በማካሄድ ለጤና ስርዓቱ በቂና ሳይንሳዊ ማስረጃዎች ለማቅረብ ይቻል ዘንድ የተጠናከረ እቅድ መኖር አስፈላጊ መሆኑ ተገለጸ።

ዶ/ር ጽጌሬዳ ክፍሌ የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር በተጀመረው የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከክልል የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እና ከክልል የጤና ቢሮዎች ጋር በሚመክርበት የጋራ እቅድ ዝግጅት ስብሰባ ላይ በመገኘት ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር ላይ እንዳስገነዘቡት ውጤታማ መሆን የሚቻለው በጋራ መስራት ሲቻልና ያለውን ውስን ሀብት በጋራ መጠቀም ሲቻል እንደሆነ አስረድተዋል።

በአሁኑ ወቅት በአለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተው የኮቪድ ወረርሽኝ በሽታን ጨምሮ ሌሎች ተላላፊ የሆኑ እንደ ኮሌራ፣ ቢጫ

. . .ወደ ገጽ 2 ዞሯል

. . . የጤና ስርዓቱን

. . .ከገጽ 1 የዞረ



ወባ፡ ደንጉ ፌቨር እና ሌሎችም አደጋዎች የአገራች የጤና ስጋቶች በመሆን የቀጠሉ በመሆናቸው በአጽንኦትና በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ ዋና ዳይሬክተርዋ አስታውቀዋል።
ዘመናዊ ህክምናን በሰለጠነ የሰው ሃይልና በዘመናዊ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች በማደራጀት ወረርሽኞችን በላቦራቶሪ በማረጋገጥ፣ የህክምና አገልግሎቱን ጥራት ባለው የላቦራቶሪ ምርመራ ለመደገፍ እንዲሁም ጥናትና ምርምሮችም በላቦራቶሪ የተደገፉ ለማድረግ የሁሉም ርብርብ የሚጠይቅና ያለውን ሀብት (የሰው፣ የገንዘብ እና የማቴሪያል) በጋራ በማቀናጀት እንደ ሀገር ውጤታማ ስራዎችን መስራት እንደሚያስፈልግ ዶ/ር ጽጌሬዳ አያይዘው ተናግረዋል።
ለሶስት ቀናት በሚቆየው ስብሰባ ላይ ጥናታዊ ጽሁፎችን ከማዘጋጀት ባሻገር በየአካባቢው ቋንቋ በመተርጎም ለችግር መፍትሔዎች አድርጎ መጠቀም ስለሚቻልበት መንገድ፡ ለወረርሽኞች ቅድመ ዝግጅት በማድረግ፣ ቅኝትን በማጠናከር፣ ቅድመ ማስጠንቀቂያ በመስጠትና አፋጣኝ ምላሽ መስጠትን በተመለከተ፤ ለኮቪድ 19 ሶስተኛ ዙር ማዕበል ምላሽ ትኩረት በመስጠትና ህብረተሰቡን የማንቃት ስራ ማጠናከርን በተመለከተ፤ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች አስተዳደር ስርዓትን ማጠናከር ስራዎችን አስመልክቶ፡ የላቦራቶሪዎችን ጥራት መጨመር ትርጉም ባለው መልኩ ትራንፎርም በሚያደርግበት መልኩ የእቅዱ አካል ማድረግን በተመለከተ፤ የአዳዲስ ምርመራዎችን ማስፋፋት ስራዎችን በተመለከተ እንዲሁም በየጊዜው ወደ ክልሎች የሚላኩ በጀቶችን ቶሎ ማወራረድ አስመልክቶ እና ዲጂታላያዜሽን በተመለከተ በትኩረት የጋራ እቅዱ አካል እንዲሆኑና እንዲታዩ ዋና ዳይሬክተርዋ አሳስበዋል።
በእለቱ በ2013 ዓ.ም የተከናወነው የተቀናጀ ድጋፋዊ ሱፐርቪዠን የተዘጋጀው ሪፖርት እና ለየክልሎች በየዓመቱ የሚላከው ፋይናንስ በተመለከተ በተገቢው ቦታና ጥቅም ላይ መዋሉና መወራረዱን በተመለከተ ሪፖርት ቀርቦ ውይይቶች ተካሂዶበታል።

## የብሄራዊ የጤና መረጃ አስተዳደር፤ ቅመራና ትንተና ማዕከልን እያከናወናቸው የሚገኙትን ተግባራት አስመልክቶ ከማዕከሉ ሃላፊዎች ጋር የተደረገ ቃለመጠይቅ





ጥያቄ- እስኪ ከአመሰራረቱ እንጀምር...አመሰራረቱ ምን ይመስል ነበር?
ዶ/ር ዓለምነሽ/ዶ.ር/አወቀ -ማዕከሉን ለመመስረት የተለያዩ ጥረቶችና ቅድመ ዝግጅቶች የተጀመሩት ከአራት ዓመት በፊት ነው።ዋናው መነሻ የጤና መረጃ አያያዝ ስርዓት ስትራቴጂ ዶክመንቱ ላይ የተነሳው ችግር ነበር፤ይሄውም የዳታ አያያዝና አጠቃቀም ችግር በተለይም የዳታ ጥራትና ተደራሽነት ችግር መኖሩ ተጠቅሶ ነበር።ዳታዎች ለፖሊሲና ፕሮግራም ቀረፃ ውሳኔዎች በሚያግዝ መልኩ ተተንትነውና ተቀናብረው አይቀርቡም ስለሆነም የመረጃ አብዮት ያስፈልጋል የሚል አቅጣጫ ተያዘ።አገራዊ

# የብሄራዊ የጤና መረጃ አስተዳደር፤.....ቃለ መጠይቅ

ተጨባጩን ስንመለከት የጤናው ዘርፍ የሚፈልገውን ዳታ በዘርፉ ለሚወጡ ፖሊሲዎች ግብዓትነት ተንትኖና ቀምሮ የማቅረቡ ልምድ አልነበረም።ዳታዎች ጥራትና ወቅቱን በጠበቀ መንገድ አይሰበሰቡም፤አይቀመጡም፡፡ ኢንስቲትዩቱ በዚህ ረገድ ራሱን ሲፈትሽ በዳታ አያያዝና አስተዳደር ላይ ትልቅ ድክመት እንደነበረበት ታይቷል።ኢንስቲትዩቱ ራሱ ያሰራውን ጥናት ለምኖ ነው ዳታ የሚቀበለው። ኢንስቲትዩቱ የጤና ሚኒስቴር የምርምርና ጥናት ክንፍ ቢሆንም ከተቋሙ የሚፈለገውን የዳታ ትንተናና ቅመራ ማቅረብና ለፖሊሲ ግብዓት መጠቀም የሚያስችል አቅም አልፈጠረም ነበር፡ በመሆኑም የጤና ነክ ዳታዎች የመረጃ ቋት ለማቋቋም ነው ይህ ማዕከል የተመሰረተው።

ጥያቄ- ማዕከሉን ለመመስረት ዋና ዋና ምክንያቶች ምን ነበሩ?

ዶ/ር ዓለምነሽ-ለማእከሉ መመስረት በርካታ ገፊ ምክንያቶች ነበሩ፤በተለያዩ አካላት የሚሰበሰቡ ዳታዎች ወደ አንድ ቋት መጥተው ለሚፈለገው ጥቅም የሚውሉበት ሁኔታ አልነበረም።አገራችን ላለፉት ሃያና ሃምሳ ዓመታት ምን ያህል የጤና ዳታ ሃብት እንዳላት አይታወቅም፤እነዚህ ሃብቶች የት እንዳሉ፤በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉም አይታወቅም፤የዳታ ሃብት አያያዝ፤ አጠቃቀም፤ዳታዎቹ ለሚፈለገው ጥቅም እንዲውሉ የተማከለ የትንተናና ቅመራ አሰራርም የለም፤የዳታ ፍሰትና ልውውጥን በተመለከተም የማስተዳደሪያ ስርዓትም አልነበረም፡፡ኢንስቲትዩታችን የጤና ሚኒስቴር የጥናት ክንፍ ቢሆንም ጤና ነክ የሆኑ አገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ሲወጡ ደጋፊ የሆኑ ጥናታዊ ማስረጃዎችን በማቅረብ ግብዓት የመስጠት ጥረቶች ብዙም አመርቂ አልነበሩም።አንድ ጥናት ተሰርቶ ካለቀ በሁዋላ በቴክኒካል ሪፖርትና በተወሰኑ ህትመቶች ላይ የተገደበ ነበር ልምዱ፤ ስለዚህ ሳይንሳዊ ዘዴን ተጠቅሞ የላቀ የቅመራ ቴክሎጂን መሰረት አድርጎ መረጃ ማምረት ላይ ያለውን ክፍተት ለመሙላት ዓላማ አድርጎ ነው ማዕከሉ የተቋቋመው።

ጥያቄ-ማዕከሉ ምን አይነት ስራዎችን ለመስራት እንደተቋቋመ ትንሽ ዘርዘር አድርገው ቢያብራሩልን?

ማዕከሉ የተቋቋመው በሀገሪቱ እስካሁን የተሰሩትን እና ወደፊትም የሚሰሩትን የጤናና ጤና ነክ ጥናትና ምርምር፤የጤና አገልግሎት፤እንዲሁም የቅኝትና ሌሎች የጤና ዴታዎችን ከተለያዩ ምንጮች በማሰባሰብ፤በመረጃ ቋት የማስቀመጥ ስራዎችን ይሰራል፡ ፡አገራዊና አህጉራዊ የህብረተሰብ ጤና ክስተቶች በተመለከተ የዳታ ልውውጥ ስርዓት ለመዘርጋት ይሰራል፤የጤና ዳታ/መረጃ የማጋራትና ስርዓት የመዘርጋት፤ የመረጃ ደህንነትና ሚስጥራዊነትን መጠበቅ ስራዎችንም ይሰራል፤የተለያዩ የዳታ ስርዓቶችን ለማናበብና መስተጋብር የመፍጠር ስራም አንዱ ዋና ትኩረቱ ነው። ከዚህ በተጨማሪም የመረጃ ጥራትና ተደራሽነትን ለማረጋገጥ ስርዓት የመዘርጋት ዓላማም ይዞ ነው እየሰራ ያለው። ይህ ብቻ ሳይሆን የጤና መረጃ ስርዓቱን ማዘመንና የዳታ ተደራሽነት የማሳለጥ ስራን የሚያከውን ሲሆን፤የላቀና ዘመኑን የዋጀ የረቀቁ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የጤና ዴታ ቀመርን ከፍተኛ ደረጃ ለማድረስ ይሰራል። በሌላ በኩል የስታትስቲክስና የሂሳብ ቀመሮችን እንዲሁም ዳታ ሳይንስ (Data Science) በመጠቀም ለጤናው ዘርፍና ለህብረተሰብ ጤና ገላጭ የሆኑ ቀመሮችን ሰዎች በቀላሉ በሚረዱት አቀራረብና መረጃውንም በቀላሉ የሚያገኙበትን የሞዴሊንግ ትንበያ ስርዓትን በመዘርጋት ተደራሽ የማድረግ ስራዎችም ይሰራል።በተጨማሪ በአገር አቀፍ ደረጃ ጤናና ጤና ነክ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በመከታተል በመገምገምና ከፍተኛ ጥራት ያላቸዉ ሳይንሳዊ ትንተናዎችን ያዘጋጃል፤ እንዲሁም በሃገሪቱና በክልሎች ውስጥ ያለውን የበሽታ ምጣኔ በዕድሜ፣ በፆታና በአመት በማጥናት ማስረጃን መሰረት ያደረገ ውሳኔ ሰጪነት ላይ ያለዉን ክፍተት ለማጥበብ ይሰራል።

ጥያቄ- ማዕከሉ ከተቋቋመ በሁዋላ ምን ተግባራትን አከናወነ?

ማዕከሉን ስራ ለማስጀመር ጠንካራ የመረጃ ትንተናና የቅመራ ቡድን ማዋቀር አስፈላጊ ነበር፡ ፡ ቡድኑን ከማዋቀር በተጨማሪ በዩኒቨርሲቲዎች፤በአጋር ድርጅቶች፤በሴክተር መስሪያ ቤቶች፤ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተሰሩትን ዳታዎች ፈልጎ ማግኘት፤ምን አይነት ዳታ እንዳለ ማወቅና ማሰባሰብ ሌላው ስራ ነበር።እስካሁን በማዕከሉ የተሰራው የዳታ ሃብትን ማወቅ፤ምን አይነት ዳታ እንዳለ መለየት፤ የት እንዳሉ ማሰስ፤በምን አይነት አያያዝ ላይ እንዳሉ ማጥናት፤ ፤ለትንትናና ለቅመራ የሚያስፈልጉ ዘመኑን የዋጀ የቴክኖሎጂ አሰራርን በማጥናት ላይ ሰፊ ስራ ተሰርቷል።ከዚህ በተጨማሪም ዳታዎቹን ከአንዱ ወደአንዱ ለማስተላለፍ የዳታ-ማጋሪያና መቀባበያ ግልጽ መመሪያዎችን ማዘጋጀትም ይጠይቅ ነበርና በርካታ የአሰራር መመሪያዎች ተዘጋጅተዋል። በሌላ በኩል በተለያየ ዘርፍና ሙያ የሚገኙና ብቃትና እውቀት ያላቸው በዘርፉ የሰለጠኑ ባለሙያዎች በመፈለግ ቡድኑን በሰው ሃይል የማጠናከር ስራ ተሰርቷል።

ጥያቄ- በአገራችን በተለይ ከጤናና ጤና ነክ ዳታዎች ጋር በተያያዘ ከዳታ አያያዝና አስተዳደር ጋር የሚነሱ ዋና ዋና ችግሮች ምን ነበሩ?

ዶ/ር ዓለምነሽ - ይታዩ የነበሩ ችግሮችን በሶስት ከፍለን ልናያቸው እንችላለን።የመጀመሪያው የሚሰሩ ምርምሮችና ዳታዎች በተመለከተ የመረጃ ልውውጥ ልምድ አለመኖሩ ተጠቃሽ ነው።ለምሳሌ አንድ ጥናት ከተሰራ በሁዋላ የዳታ ባለቤትነት ጉዳይ ሲነሳ የሚሰሩ ጥናቶች የኢንስቲትዩቱ ሳይሆን የተመራማሪው የራሱ የግሉ ንብረት አድርጎ የማየት ልምድ

. . .በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል